# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የመ/ሠ/ቁጥር 184647

ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው
ተሾመ ሽፈራው
ሀብታሙ እርቅይሁን
ብርሃኑ መንግሥቱ
ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ፍስሀ አበበ

ተጠሪ፡- አቶ አለነ ደሞዝ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለው የፍርድ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየበት በትግራይ ክልል በፀለምቲ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የከሳሽ ተጠሪ ደግም ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ከክርክሩ እንደተረዳነው ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረተው ክስ በማይ ተክሊት ቀበሌ አዲስ በተመሰረተችው በማይ ተክሊት ከተማ ለመኖሪያ ተብሎ በ1994 ዓ/ም ተሰጠኝ ስፋቱ 10×15 ሜትር በሆነ ቦታ ያለኝን አንድ ክፍል ቤት የመኖሪያ ቤትና ቦታ በ2000 ዓ/ም ለአሁን አመልካች በብር 7700.00 (ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ብር) ሸጬለት የነበረ ቢሆንም መሬት ስለማይሸጥ ከመነሻው የፈረሰ ውል ነው፡፡ ቤቱን ሲገዛ የከፈለዉን ብር 7700.00 ደግሞ በኪራይ መልክ አመልካች እያከራየ ወስዶ ጨርሷል፡፡ ነገር ግን አመልካች በዚሀ ይዞታዬ ላይ 5×5 ሜትር የሆነ ቤት ሰርቶበት ይዞ አለቅም ስላለኝ በይዞታው ላይ የተሰራውን ቤት አፍርሶ መሬቱን እንዲለቅልኝና ከቤቱ ጋር የተረከባቸዉን ንብረቶች ዋጋ በግምት ብር 5500.00 እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ በ1999 ዓ/ም ከአንድ ክፍል ቤት ጋር በብር 7700.00 መኖሪያ ቤትና ቦታ ከገዛሁ በኋላ 2 ትላልቅ በግንብ የተሰራ ዘመወናዊ የቆርቆሮ ክፍል ቤቶችን ከብር 360,000 በላይ ወጭ አዉጥቼ ስለሰራሁ ዉሉ ወደነበርንበት ይመለስ ከተባለ በጣም ስለሚጎዳኝ የሽያጭ ውሉ ይፅናልኝ፡፡ ባንኮኒ ከቤቱ ጋር የገዛሁት ነዉ፡፡ ሌሎች ንብረቶችን ስላልተረከብኩ ግምት ልከፍል አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ስልጣን ያየው የወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 13075ላይ አከራክሮና ምስክሮታቸዉን ሰምቶ በቀን 22/09/2011 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 40/7 መሰረት መሬት የሕዝብና የመንግስት ሀብት በመሆኑ ለመሸጥ ለመለወጥ ስለማይቻል በግራ ቀኝ መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ሕገ መንግስቱን የሚቃረን በመሆኑ የሽያጭ ዉሉ እንዲፈርስና አመልካች የሰራዉን ቤት አፍርሶ እንዲወስድ

*በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 12167 ላይ በቀን 07/10/2011 ዓ/ም በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥ 337 መሰረት በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዟል።*

*በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ችሎቱ በመ/ቁጥር 117434 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 21/10/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክስ ሲያቀርብ ማይ ተህሊት ቀበሌ አዲስ የተመሰረተች አተማ እንደሆነች በመግለጽ አመልካች በዚህ ከተማ የሚገኝ የመኖሪያ ቤትና ቦታ ይልቀቅልኝ በማለት ዳኝነት ቢጠይቅም በስር ፍርድ ቤት አዲስ የተመሰረተች ከተማ ናት ወይስ አይደለችም የሚለው አልተጣራም። በተጨማሪ ተጠሪ በክሱ ውስጥ አዲስ የተመሰረተች ከተማ መሆኗን ቢገልም እንኳን በተግባር ግን ከ1ኛ እስክ 3ኛ ደረጃ ባሉት ከተሞች ማይ ተኽሌት አዲስ የተመሰረተች ከተማ ሆና በአዲስ ከተማነት የተካተተች አለመሆኗ ተረጋግጧል በማለት የሻያጭ ዉሉ የገጠር መኖሪያ ቦታ ሽያጭ የሚመለከት በመሆኑ ዉሉ ሕገወጥ ነው ተብሎ አመልካች የሰራዉ ቤት ካለ አፍርሶ ይውሰድ በሚል በስር ፍርድ ቤት መወሰኑ ተገቢ ነዉ በሚል በማፅናት ነገር ግን አመልካች ቦታዉን የገዛበትን ብር 7700.00 ተጠሪ እንዲመልስ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል ። አመለካች በቀን 30/01/2012 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ በዚህ አግባብ በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ የሚከተለዉ ነዉ።*

*አመልካች የገዛሁት የገጠር መሬት ሳይሆን ለተጠሪ በከተማ ለድርጅት ተብሎ በተሰጠዉ ቦታ ላይ የተሰራ ቤት ከነ ይዞታው ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች የገጠር መሬት አይሸጥም ብለዉ ከሚያከራክረን ጭብጥ ዉጭ ውሳኔ ሰጥተዋል። በግራ ቀኙ የቀረቡ ምሰክሮች የተረጋገጠዉም በከተማ የተሰራ ቤት የተሻሻጥን መሆኑን ነዉ። ቤትና ቦታዉን መልቀቅ አለብህ የሚባል ከሆነ ተጠሪ ፈቅዶ እና ሳይቃወመኝ 2 ትላልቅ ቤቶች ብር 360000.00 የሚገመት ስለሰራሁበት በፍ/ሕግ ቁጥር 1179/2/ መሰረት የዚህን ግምት እና የቤቱን የግዢ ዋጋ ብር 7700.00 ተጠሪ ከወሰደበት ከቀን 12/05/1999 ዓ/ም ጀምሮ በሚታሰብ ህጋዊ ወሊድ ጋር እንዲከፍለኝ አለመወሰኑም መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረም ዘበመጠየቅ እቤቱታዉን አቅርቧል። የሰበር አጣሪ ችሉት እቤቱታዉን መርምሮ በዚህ ጉዳይ የሻያጭ ዉሉ የተደረገዉ በከተማ ይሁን በገጠር ባልተለየበት እና አመልካች ቤትና ይዞታ ገዛሁ በማለት እየተከራከረ ዉሉ ፈርሶ የገነባዉን ቤት አፍርሶ ይልቀቅ ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1731 እና 1179 አንጻር ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ቻሎት ያስቀርባል ብሎ ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 02/06/2012 ዓ/ም የተፃፈ የአጭሩ የሚከተለውን መልስ አቅርቧል።*

*አመልካች በቦታው ላይ 360000.00 ወጭ እድርጌበታለሁ ይበል እንጂ የተሰዉ ቤት በሁለት ገጽ የድንጋይ ካብ ሲሆን በሁለት ገፅ ደግሞ ግድግዳ እና በ25 ቆርቆሮ ሁለት ቢያጆ ድንጋይ እና ግድግዳው የገጠር እንጨት ነው። ይህም በትክክል ቢገመት የወጣዉ ወጪ ከብር 6000-7000 ቢሆን ነዉ። ቦታዉ የገጠር መሬት ስለሆነ አይሸጥም አይለወጥም። ውላችን በ2000 ዓ/ም ፈርሶ ቤቱን የሰጠኝን ገንዘብ እራሴ በቦታው የስራሁትን ቤት እያከራየ እንዲወስድ ተስማምተን ገንዘቡን መዉሰዱን በወረዳ ፍርድ ቤት በምስክሮች ተረጋግጧል። ቤቱንም ከሁስት አመት በፊት ለቆ አስረክቦኛል። ግምት እንኳ መፈል ካለብኝ*

*የገጠር ቦታ ስለሆነ በሽማግሌዎች የተገመተውን ብር ውሰድ ብዬው ፈቃደኛ አይደለም። ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤቶቻ የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ተብሎ አቤቱታዉ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክራል። አመልካች በቀን 21/06/2012 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክራል።*

*ከዚህ በላይ የተመዘገበዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆንእኛም ሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ በሰበር ችሎት ያስቀርባል ብሎ ከያዘዉ ጭብጥ አንጻር በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን ከግራ ቀኝ ክርክር፥ ከስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔዎች ይዘት እና አግባብነት ካለዉ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብእንደሚከተዉ መርምረናል።*

*እንደመረመርነውም ግራ ቀኙን ያከራከረዉንና የዚህን ችሎት ውሳኔ የሚፈልገዉ ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሰረተው ክስ የጠየቀዉ ዳኝነት ከአመልካች ጋር አዲስ በተመሰረተችዉ ማይ ተኽሊት ከተማ ዉስጥ ለመኖሪያ ተብሎ በ1994 ዓ/ም በተሰካጠዉ ቦታ ላይ የተሰራዉን አንድ ክፍል የመኖሪያ ቤትና ቦታ ለአመልካች በ1999 ዓ/ም ስለሸጥኩ መሬት መሸጥና መለወጥ ስለማይቻል ዉሉ ከመነሻዉ ፍርስ(void) ስለሆነ አመልካች በይዞታው ላይ የሰራውን ቤት አፍርሶ መሬቱን እንዲለቅልኝይወሰንልኝ በሚል የጠየቀዉን ዳኝነት በተመለከተ የተሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ። አመልካች ከስር ጀምሮ የቤት ሽያጭ ዉሉ ባዶ መሬት ለመግዛት የተደረገ እንዳልሆን እና በቦታዉ ላይ ከፍተኛ ገንዘብአዉጥቼ ተጠሪ ሳይቃወመኝ ተጨማሪ 2 ክፍል ቤቶች ስለሰራሁ ውሉ ሊፈርስ እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል። የክልሉ ፍርድ ቤቶች በግራ ቀኝ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ዉል እዲፈርስ የወሰኑት ዉል የተደረገዉ በሕገ መንግስቱ የተከለከለዉን መሬት እንዳይሸጥ የተደነገገዉንክልከላ በመተላለፍ የተደረገ በመሆኑ የዉሉ ጉዳይ ሕገወጥ ነዉ በማለት እንደሆነ ተገንዝበናል።*

*እንደሚታወቀው በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት እና በተመሳሳይ በትግራይ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/3 ስር የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የሕዝብ ብቻ በመሆኑ መሬት  የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት መሆኑ በግልጽ ተደንግጓል። በዚህ መሰረት በገጠርም ሆነ በከተማ ባዶ መሬት በመሸጥ የሚፈጸም ዉል ሕገመንግስታዊ የሆነዉን መሬት አይሸጥም የሚለዉን ክልከላ የሚጥስ በመሆኑ የጸና ዉል እንዲኖር አስፈላጊ ሁኔታ ተደርጎ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1678/ለ ስር የተደነገገዉን የዉሉን ጉዳይ ሕጋዊ የመሆን ሁኔታ የማያሟላ ስለሚሆን በፍ/ብ/ሕግ/ቁጥር 1716 እና 1808/2 ስር በተደነገገው መሰረት ዉሉ የተደረገበት ጉዳይ ከሕግ ዉጭ ስለሆነ ከመነሻዉ ዋጋ አልባ ዉል እንደሆነ የሚቆጠር ወይም ደግሞ ዉሉ ፈርሷል ተብሎ በፍርድ እንዲነገር ጥቅም አለኝ በሚል ሰዉ ተጠይቆ እንዲፈርስ ሊወሰን ይችላል።*

*በሌላ በኩል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስትም ሆነ በተመሳሳይ በትግራይ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 40/7 ስር እንደተደነገገዉ ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ከመሬት ላይ ለሚገነባዉ ቋሚ ንብረት (የማይንቀሳቀስ ንብረት) ወይም ለሚያደርገዉ ቋሚ*

መሻሻል ሙሉ መብቱ እንደሰጠዉና ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማዉረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱንየማንሳት፣ ባለቤትነቱን ማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን የሚያካትት እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ከሺያጭ ጋር በተያያዘ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/3 እና 40/7 ስር ከተደነገገዉ በግልጽ የምንረዳዉ የተከለከለዉ ተግባር የገጠርም ሆነ የከተማ ባዶ መሬት እንዳይሸጥ እንጂ ማንም ኢትዮጵያ'ዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ የገነባዉን ቋሚ ንብረት (ለምሳሌ ቤት) መሸጥ ወይም ባለቤትነቱን ማዛወር የተከለከለ ተግባር አይደለም፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በመሬት ላይ ጉልበቱን ወይም ካፒታሉን(ገዝቡን) በማፍስስ የሚገነባዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (1እና2) ስር በተደነገገዉ መሰረት ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ የሚደረግለት የግል ንብረት በመሆኑ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ለአመልካቸ በሺያጭ ያስተላለፈዉ ባዶ መሬት ነዉ የሚል ክርክር በግራ ቀኙ አልቀረበም፡፡ የተሸጠዉ የከተማም ሆነ የገጠር ባዶ መሬት ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃም ቀርቧል በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠና በዉሳኔዎቻቸዉ ላይ የተገፀጸ ነገር የለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪራሱ በክሱ ላይ የገለጻዉ ፍሬ ነገር የሚያሳየዉ በሺያጭ የተላለፈዉ ቤት አዲስ በተመሰረተችዉ ማይ ተኽሊት በተባለች ከተማ ተጠሪ መኖሪያ ቤት እንዲሰራበት በተሰጠዉ 10x15 ሜትር በሆነ ቦታ ላይ የሰራዉን አንድ ክፍል ቤት መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤት የ'ተሰየሙት የግራ ቀኝ ምስክሮች ከዚህ የተለየ ነገር ስለመመስከራቸዉ አልተረጋገጠም፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉ ተጠሪ ለአመልካች በሺያጭ ያስተላለፈዉ የግል ንብረቱ የሆነውን ቤት እንጂ ባዶ ቦታ አለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ እንዲሁም ማንም ኢትዮጵያዊ በመሬት ላይጉልበቱን ወይም ካፒታሉን(ገንዘቡን) በማፍሰስ የሚገነባዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት የግል ንብረቱ በወመሆኑ በሺያጭለማስተላለፍ የሚያስችል ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ የተደረገለት መብት ያለዉ መሆኑ በፌዴራልም ሆነ የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40{1 ፣2 እና 7) ስር የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪም ይህንኑ መብቱን በመጠቀም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በሺያጭ ለአመልካች ማስተላለፉን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ አግባብ ባዶ መሬት በሕጋዊ መንገድ በማግኘት በመሬቱ ላይ ቤት በመመስራት የሚደረግ የቤት ሺያጭ ውል ሕገ መንግስቱንም ሆነ ሌሎች ሕጎችን ይቃረናል የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ በግራ ቀኝ መካከል የተደረገዉ የቤት ሺያጭ ዉል ጉዳይ ከህግ ዉጭ ነዉ ተብሎ እንዲፈርስየሚወሰንበት የሕግ መሰረት የለም፡፡

ሲጠቃለል የሺያጭ ዉሉ ላይ የተመለከተዉ የዉሉ ጉዳይ የከተማም ሆነ የገጠር ባዶ መሬት በሺያጭለማስተላለፍ የተደረገ ካልሆነ በስተቀር ማንም ኢትዮጵያ በመሬት ላይ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡየገነባዉን ቤት (የማይንቀሳቀስ የግል ንበረት) በሺያሽጭ ለማስተላለፍ የሚያስችል ሕገ መንግስታዊ ጥበቃ ያለዉ መብት በመሆኑ በመሬት ላይ የተገነባን ቤት ለመሸጥ የሚደረግ ዉል ጉዳይሕገወጥ ነዉ ሊባል የሚቻል አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለግራ ቀኝ ክርክር መነሻ የሆነዉን የቤት ሺያጭ ዉሉን ጉዳይ ሕገ መንግስቱን ስለሚቃረን ሕገ ወጥ ነዉ በማለትመወሰናቸዉም ሆነ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ የጽና የቤት ሺያጭ ዉል ነዉ በማለት ዉሉ ሕገ ወጥ ስለሆነ ዋጋ አልባ ነዉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመዉን ስህተት ማረም ሲገባዉ በአብላጫ ድምጽ ዉሳኔ የተሸዉ ቤት ቤት አዲስ በተመሰረተከተማ ዉስጠ እንደሚገኝ በተጠሪ ክስ ላይ በግልጽ እያለና ይህንን የሚያስተባብል ማስረጃ በተከራካሪ

*ወገኖችም ሆነ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ባልቀረበበት በገጠር የእርሻ መሬት ላይ ቤት ተሰርቶ ከሕግውጭ በሆነ አኳኋን የሽያጭ ዉል እንደተፈጸመ በመቁጠር የቤት ሽያጭ ዉሉ ጉዳይ ከሕግ ዉጭ ነዉ በማለት እንዲፈርስ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራርና የሕግ አተገባበር ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል።*

## ዉሳኔ

*1. የፀለምቲ ወረዳ ፍርድ ቤት ቡመ/ቁጥር 13079 ላይ በቀን 22/09/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ውሳኔ፤ የሰሜን ምእራብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12167 ላይ በቀን 07/10/2011 ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 117434 ላይ በቀን 21/01/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 ተሽረዋል።*

*2 በግራ ቀኝ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል የጸና ነዉ በማለት ወስነናል። 3 ግራ ቀኝ በዚሁ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን እንዲችሉ ተወስኗል።*

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።*

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።*

# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ.150408

ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ
መስጠፋ አህመድ
አብርሃ መሰለ
ፈይሳ ወርቁ
ጸውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አመለወርቅ ፍቅሬ - ጠበቃ ለገሰ ማሞ -ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋሁን ታፈሰ -የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የወላይታ ሶዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በወላይታ ሶዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር በቀን 3/6/2006 ዓ.ም በተፈጸመ ጋብቻ በቁጥር 240/270//2006 በቀን 12/06/2006 ዓ.ም በብሔራዊ የጋብቻ ስነስርዓት መሰረት ከሶዶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የጋብቻ ምስክር ወረቀት ወስደው ጋብቻ ከፈጸሙ በኋላ እንደማንኛውም ባለትዳር በአንድ ጣራ ስር መኖር ሳይጀምሩ ወደ አሜሪካን አገር መሄዳቸው በመግለጽ ለአለፉት አራት ዓመታት ከተጠሪው ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳይኖር በተለያየ ቦታ የሚኖሩ መሆናቸውና ልጆች ሆነ የጋራ ሀብት ያላፈሩ በመሆኑ በመካከላቸው ያለው ጋብቻ ፈርሶ የፍቺ ውሳኔ እንዲወሰንላቸው ተጠሪው ላይ ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም ለቀረበው ክስ የሰጡት መልስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በህግ የፀና ጋብቻ ስለመኖሩ ሳይክዱ በጋብቻ ውስጥ መኖራችን ጥያቄ ማንሳት የሚችሉት ተጋቢዎች ወይም አንዳቸው እንጂ ሌላ ሰው የሚያነሳው ሀሳብ የህግ ድጋፍ የሌለው በመሆኑ ስለተጋቢዋ ሆኖ ጠበቃ የፍቺ ጥያቄ ማቅረብ የማይችል ስለሆነ ክሱ ወድቅ እንዲደረግ ይህ መቃወሚያ የሚታለፍ ከሆነ በህጉ መሰረት የሞራል

ካሳ ተወስኖ የወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አማራጭ መከላከያ መልሳቸው በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም በቀረበው መቃወሚያ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በቀን 4/3/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካች ወንድም አስቀድሞ የተጻፈ

ሕጋዊ ውክልና ሰነድ ሳይኖር አመልካችን ወክሎ የአመልካች ጋብቻ እንዲፈርስ ጠበቃን የመወከል መብት በህጉ አልተሰጠውም፤ ስለሆነም በተጠሪ የቀረበው መቃወሚያ ተገቢ ሁኖ ስለአገኘን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 33/2/ እና 244/መ/ መሰረት የአመልካች ተወካይ ነኝ ባይ ክሱን ለማቅረብ መብት የለውም ሲል ብይን ሰጥቷል። ይህንን ብይን በመቃወም የአመልካች ተወካይ ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት ሳያገኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ሰርዞታል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካች ታህሳስ 4 ቀን 2010 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለወንድማቸው የሰጡት ውክልና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ቀርቦ ባለበት የተሟላ ውክልና አልቀረበም በሚል ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው በማለት በአመልካች የቀረበው አቤቱታ ከውክልና አንፃር ለመጣራት ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዙት መሰረት የካቲት 21 ቀን 2010 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካች ጠበቃ በተጠሪ የቀረበው መልስ ላይ የመልስ መልስ መስጠት የማይፈልጉ መሆኑን በመግለጻቸው ምክንያት የቀረበ የመልስ መልስ የለም።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል። በመሰረቱ በመርህ ደረጃ የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚገባው ከባልና ሚስቱ አንደኛው ተጋቢ ወይም ሁለቱም ቢሆንም በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው ውክልና ማስረጃ ጋር የሚቀርብ የፍቺ ጥያቄ በህግ የተከለከለ አይደለም። ከባልና ሚስት አንዳቸው የፍቺ ጥያቄ እስካቀረቡ ድረስ ፍቺው ሊከለከል እንደማይቻልና ፍቺ ሊወሰን አይገባም የሚለውን ነጥብ መሰረት በማድረግ ብቻ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ እንደማይቻል በተሻሻለው ፌዴራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 112 ሆነ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 አንቀጽ 127 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። በሌላ በኩል ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሁኖ ካገኘው ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሊያነጋግር ወይም ጉዳዩን ሲመረምርና ምስክር ሲሰማ በዝግ ችሎት ያስችላል የሚለውን የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌ/አንቀጽ 110/ በመጥቀስ ጋብቻና ጋብቻ ፍቺ በውክልና ሊቀርብ አይችልም በማለት በተጠሪ የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም። ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ተጋቢዎችን የሚያነጋግራቸው አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ እንጂ የግድ ማናጋገር እንዳለበት የሚደነግግ ባለመሆኑ፤ ጋብቻ በእንደራሴ መፈጸም በመርህ ደረጃ የማይቻል ቢሆንም ከተጋቢዎች አንደኛው ጋብቻው ለመፈጸም ፈቃዱን በሚያሻማ ሁኔታ በመግለጽ በግንባር ለመገኘት የማያስችለው ከባድ ምክንያት

ሲያጋጥመው ጉዳዩ ለፍትህ ሚኒስትሩ ቀርቦ ሲረጋገጥ ጋብቻውን በእንደራሴ አማካኝነት መፈጸም እንደሚቻል በግልጽ በተሻሻለው ፌዴራል ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 12 ተደንግጓል።

ጋብቻ ለመፈጸም በልዩ ሁኔታ በውክልና እንደሚቻል ህጉ እየፈቀደ የፍቺ ጥያቄ በውክልና ሊቀርብ አይችልም በማለት በተጠሪ በኩል የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም። እዚህ ሊታይ የሚገባው ነጥብ የውክልናው ማስረጃ ህጋዊነት ነው። ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት የአመልካቹ ወኪል ሆነው የቀረቡት ሰው በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር በተሟጋችነት ሊቆሙ ስለሚችሉ ሰዎች በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለው ጥያቄ ነው።

በመሰረቱ በማናቸውም ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ለመከራከር ባለጉዳዩ ራሱ እንዲቀርብ የሚያስገድድ ሕግ ወይም በፍርድ ቤቱ የተሰጠ የተለየ ትዕዛዝ የሌለ በሆነ ጊዜ ባለጉዳዩ ራሱ ለመቅረብ የማይችል ወይም የማይፈቅድ ሲሆን ነገሩን ለማስረዳት፣ ለመከራከር፣ለሚጠየቀው ሁሉ በቂ መልስ ለመስጠት የሚችል ሰው በዋናው ባለጉዳይ ተተክቶ በነገረ ፈጅነት፣በወኪልነት፣በጠበቃነት እንዲከራከር ለማድረግ እንደሚችል በፍ.ስ.ስ.ሕ.ቁ.57 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ሕግ በቁጥር 60፣61 እና 62 ስር የተመለከቱት ልዩ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አበል ሳይሰጣቸው ስለሌላ ሰው ሆኖ በወኪልነት ወይም በነገረ ፈጅነት አቤቱታ ለማቅረብ፣ ለመከራከር፣ ለመሟገት እና ነገሩን ለመከታተል የሚችሉት የዋናው ባለጉዳይ ባለቤት፣ወንድም፣እህት፣ልጅ፣አባት ወይም አያት ስለመሆናቸው በቁጥር 58(1) ስር ተመልክቷል። በተያዘው ጉዳይ ስለአመልካቹ በመሆን ውክልና የተሰጣቸው የአመልካች ወንድም በመሆናቸው ከዋናው ባለጉዳይ ጋር በቁጥር 58(1) ከተመለከተው የዝምድና ግንኙነት መካከል አንዱን የሚያሟሉ ስለመሆኑ አከራካሪ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን የውክልና ሰነድ ከውጭ ሀገር ተዘጋጅቶ የተሰጠ በመሆኑ ከሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንጻር መመርመሩ ተገቢ ሁኖ አግኝተነዋል። ከኢትዮጵያ ውጭ የተዘጋጁ ሰነዶች ትክክለኘነታቸው በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 922/2008 አንቀጽ 1፤6፤23 እና 24 ድንጋጌዎች መሰረት በኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር እና በኢፌዴሪ የፍትህ ሚንስተር የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ጽ/ቤት መረጋገጥ እንዳለበት ተደንግጓል።

አመልካች ለወንድሟቸው የሰጡት ውክልና ስልጣን በኢፌዴሪ ኢምባሲ ዋሽንግተን በቁጥር 05155/09 በቀን 14/07/2009 ዓ.ም የፊርማና ማህተም ትክክለኛነት ተረጋግጦ የተሰጣቸውን ውክልና የኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚንስተር በቁጥር 28456/10 በቀን 22/01/2010 ዓ.ም የፊርማ ማህተሙ ህጋዊነት ከተረጋገጠ በኋላ የኢፌዴሪ የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በቁጥር ቅጽ/2380/10/2010 በቀን 22/01/2010 ዓ.ም ትክክለኛነቱ የተረጋገጠና የተመዘገበ የውክልና ማስረጃ መሆኑን በተጠሪ በኩል ማስተባበያ ያልቀረበበት መሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል። የተሰጠው ውክልና ማስረጃ ይዘትም በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.58 እና በፍ/ብ/ህ/ቁ.2199 አመልካችን ፍቺን ጨምሮ በማናቸውም ጉዳዮች ወክሎ ለመከራከርም ሆነ ሌላ የህግ ባለሙያ ለመወከል እንደሚችሉ በውክልና ሰነድ ላይ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑም ተጠሪ የውክልና ማስረጃው ፍትህ ሚንስተርና ውጭ ጉዳይ ሚንስተር ቀርቦ ማህተም ተደርጎ በባለስልጣን ፊርማ ተረጋግጦ የቀረበ ባለመሆኑ ሕጋዊነት የጎደለው ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም። በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው የቤተሰብ ህጉ የጋብቻ ፍቺ ክስ በወኪል ማቅረብ የማይከልክል ሁኖ እያለ እንዲሁም አመልካች ለወንድሟቸው የሰጡት ውክልና ማስረጃ የህጉን መስፈርት የሚያሟላ ሁኖ ተወካዩ በራስቸው ወይም ጠበቃ

*በመወከል ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የሚያስችላቸው ህጋዊ ውክልና በመያዝ ያቀረቡት ክስ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።*

***<u>ውሳኔ</u>***

*1. በወላይታ ሶዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 38955 ህዳር 4 ቀን 2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወላይታ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 21387 ህዳር 19 ቀን 2010 ዓ.ም በትእዛዝ ያጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሸሯል።*

*2 የወላይታ ሶዶ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል። ይፃፍ።*

*3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።*

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።*

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።*